ሰኔ 2016
ቅፅ ፩
ቁጥር ፪

## ካለመታየት በእይታ ሲገለፅ

# ንስንስ

QUEER ETHIOPIA
ኩዊር ኢትዮጵያ

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ በኩዊር ኢትዮጵያ የምትታተም መጽሔት
Nisnis - A quarterly magazine published by Queer Ethiopia focusing on LBQ issues

# QUEER ETHIOPIA
## ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ’ ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret

# ማውጫ

የአርታዒያን
መልዕክት
2 - 3

ጥያቄ
እና
መልስ
4 - 20

# የአርታዒያን መልዕክት

በ12ኛው የንስንስ እትም በይዘት እና አቀራረብ ለየት ብለን መጥተናል።

ይህን ለየት ያለ የ“ዛይን” ይዘት ያለው መጽሄት ይዘን የመጣነው በታሪክ ለተገለሉ ማህበረሰቦች የተቃውሞ እና የደስታ መግለጫ ሆነው መቆየታቸውን ታሳቢ በማድረግ ነው። ንስንስ በ”መደበኛ” ቅርጹ፣ ሁልጊዜም ለማህበረሰባችን የራሳችንን ታሪክ ለመንገር የሚያስችል ሆኖ ቆይቷል። ይህ “ዛይን” ግን ኩራታችንን ይበልጥ አስደሳች እና ቀላል በሆነ መንገድ እንድናከብር ያስችለናል።

እንደ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ኢትዮጵያዊያን ህልውናችን የመታየት እና የመደበቅ ሚዛናችንን በመጠበቅ እና በአብዛኛው ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች በሚጠላ እና የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ እየኖርን የኛ የምንለውን የራሳችንን ማህበረሰብ ደግሞ ጎንለጎን ፈልገን የምናገኝበት ነው፣ ያለማቋረጥ መደበቅ አድካሚ ነው።

የመጽሄታችን ገጾች ግን አለመታየታችንን በኩራት ወደምንታይበት መንገድ የሚመራን ነው፣ እውነታችንን፣ ፍላጎታችንን፣ እና ከነሙሉ ማንነታችን ራሳችን ገልጸን ማህበረሰባችንን የምንገነባበት፣ ጥብቅ ግንኙነቶችን የምንፈጥርበት እና የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት ተሞክሯችንን የምናከብርበት ነው

በኩዊር ማንነታችን ውስጥ ያለውን ለስላሳነት፣ እራሳሽንን ከመቀበል የሚገኘውን ነፃነት እንዲሁም የራሳችንን ሰዎች ማግኘታችን ስናውቅ የሚሰማንን ሰላም ስናከብር ሁሉም በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት ውስጥ ያለውን ውስብስብ ውበት የሚያሳይ ነው፣ በአስቂኝ አጠባበሶች እየሳቅን፤ በሚያሳፍሩ ራስን የመግለጽ አጋጣሚዎች እየተሽኮረመምን ጥብቅ ግንኙነትን እንመሰርታለን።

ኩራታችንን ስናከብር በነዚህ ገጾች ውስጥ ያሉትን ብልሀት፣ ቀልድ እና ርህራሄን እያሰብን ይሁን፣ ራሳችንን የመሆን ደስታን እየኮራንበት የማይታይ አለማችን ውስጥ እንታይ።

መልካም ኩራት ለውብ ማህበረሰባችን! የምትስቁበት፣ የምትደንሱበት እና ከጥላቻ በላይ ከፍ ብላችሁ የምትታዩበት ዘመን ይሁን!

ለእርስዎ ወሲብ ነክ ያልሆነ ግን ስሜት ቀስቃሽ ነገር ምንድነው?


ወጣ ያለ ሊሆን ይችላል ግን ባለቤቴ ጠጠር ያሉ ቃላትን ስትጠቀም በጣም ደስ ይለኛል፣ በተለይ የማላውቀውን ቃል።

- ግሎሪያ





ለኔ መተያየት ትልቁ ወሲባዊ ያልሆነ
ስሜት ቀስቃሽ ነገር ነው፣ ኣንዳኛ
እኔ የማሽኮረምም ሰው ነኝ፣ ስለዚህ
ኣይን ለኣይን መተያየት ጥልቅና በቃላት
የማይገለጽ መቀራረብን ይፈጥራል።
- በጸሎት



## ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ ስለማንነትዎ ሲናገሩ ያገኙት አስቂኝ ምላሽ ምንድን ነው?

"እንዴት ነው ወሲብ የምትፈጽሚው?" አሁን ሳስበው እንዳሳይሽ ትፈልጊያልሽ? ብዬ መመለስ ነበረብኝ። - ስም ያልተገለጸ

ከጓደኞቼ አንዱ አንቺ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ አይደለሽም፣ ደንግል ብቻ ነሽ ብለውኛል - ሜላት

ኣዲስ ኣበባ በሚገኘው የግሪክ ክለብ ምሳ
እየበላን ለእህቴ ባል እህት ሌዝቢያን እንደሆንኩ
ነገርኳት፣ በጣም ፈገግ ብላ ኣስተናጋጁን
በደስታ ጠርታ፣ “ሌላ ማኪያቶ ኣምጣልኝ፣
እያከበርን ነው!” ኣለችው። - ሓበን




# የሚያዳንቁት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ አለ? ለምን?



ማንም የለም፣ እንዳውም ሳስበው ራሴን ነው የማዳንቀው - አቢጌል

በሁላችንም በጣም እኮራለሁ - ስም ያልተገለጸ






የምትመሳሰይውን ሰው አግኝተሽ ልምድን መጋራት መቻል ፈውስ ነው። ለአእምሮ ጤንነታችንም አስፈላጊ ነው። - ስም ያልተገለጸ

ምክንያቱም ሁላችንም የሚደግፈን ሰው እና የምንወዳውን መውደድ ምንም ችግር እንደሌለው ሊነግረን የሚችል ሰው ሊኖረን ስለሚገባ - ሜላት

ምክንያቱም በሁሉም ሰው የሚገፉ ማህበረሰብ አባል እንደመሆናችን አንድነት ፈጥረን እርስ በርስ መጠባበቅ ስላለብን። - ኬስ

ሰው አለኝ ማለት ብቸኛ እንዳልሆንኩ በርካቶች እንደሆንን - መሲ

እስካሁን ሰምተው የሚያውቁት (ወይም ራስዎ የተጠቀሙት) ምርጥ የኣጠባበስ ንግግር ምንድነው?


“በመጀመሪያ እይታ ፍቅር ታምኛለሽ ወይስ እንደገና ባጠገብሽ ልለፍ?” ቀላል፣ ዶስ የሚል እና ፈገግታ የሚያጭር ነው - በጸሎት





ስም ኣለሽ ወይስ የእኔ ልበልሽ? - ጃምዚ

“ካሜራ ነሽ? ምክንያቱም ባየሁሽ ቁጥር ፈገግ እላለሁ” እኔ ግን በፍፁም ተጠቅሜበት አላውቅም LoL) - ሜላት



የዳከመሽ ትመስያለሽ ፊቴ ላይ አረፍ ማለት ትፈልጊያለሽ? - ሪዶ

“ከአንቺ ጋር slytherin ማድረግ እችላለሁ?" ስለ ሃሪ ፖተር እያወራን ነበር - ኬስ

ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጓደኝነት የሚያደንቁት ባሕሪ ምንድን ነው?

አንድ አይነት ጾታን ስለምንወድ አንድ አይነት የፖለቲካ ንቃተ-ህሊና ወይም መርህ ይኖረናል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የሚረዱን እና ከነማንነታችን የሚቀበሉን ጓደኞች በረከት ናቸው። - ስም ያልተገለጸ



ጓደኝነቱ ጤናማ ከሆነ የተሰማኝን ሁሉ መናገር እችላለሁ፤ በምናገረው ነገር ደግሞ ኣሌገመትም - ሬዶ



በፍቅር ወይም
በወሲብ ጓደኛ ውስጥ
በጣም የሚያደንቁት
የትኛው ባህሪ ነው?




ጠንካራ ክንድ ሲኖራቸው🥵 ፤ በቀላሉ የማይደክማቸው እና ከረዥም ጨዋታ😉 በኋላም ለኔ አንድ ኩባያ ውሃ መስጠት የማይደክማቸው ሲሆኑ
- ግሎሪያ

ቤት መሆን የሚወድ ሰው። - ሬድ




## የሚወዱት የተመሳሳይ ጾታ ከፍቃሪ ፊልም ወይም መጽሀፍ ምንድን ነው?





- Rafiki
- Imagine Me & You, Below Her Mouth, Gap
- Elisa and Marcela, The L Word
- My First Summer
- Crush and Pride
- Carol, Station 19, Orange is the New Black
- The Handmaiden
- Disobedience

- Fear of Falling" by Georgia Beers
- Sister Outsider by Audre Lorde
- The Color Purple by Alice Walker
- Camren fanfics (in Wattpad)





ወሲብ እያረግን ፍሬድ መጣ፤ ልጅ ቢጤ ስለነበርኩ በጣም ነው ያፈርኩት፤ የፍሬድ ላይ ወሲብ ግን ደስ ይላል - ስም ያልተገለጸ

ለመጀመሪያ ጊዜ አንዲት ሴት squirt ስታደርግ፣ በእግሮቿ መካከል ሆኜ በጣቶቼ እያስደሰትኳት ነበር፣ እና ፊቴ ላይ ነው squirt ያረገችው፣ ደንግጬ ለጥቂት ደቂቃዎች ምን ማድረግ እንዳነበረብኝ አላወኩም፤ ሳቅን ግን በጣም አፍሬ ነበር - ሓበን



😂😂 69 የሚባለውን የወሲብ አዳራረግ እየሞከርን ነበር፤ ሁኔታው የሚያሳፍር ነበር ምን እያረኩ እንዳለሁ አልገባትም እኔ ደሞ እንዴት እንዳማስረዳት ግራ ገባኝ 😂😂 - ግሎሪያ

ከአንድ ዙር በኋላ በቃኝ አልኩ ፣ እና እሷ፣ "እንደ ተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ሰው?!" አለችኝ:: - ሪድ



ሰዎች ስለተመሳሳይ ጾታ ኣፍቃሪዎች እንዲያውቁ የሚፈልጉት ነገር ምንድነው?

የኔ ማር! ብዙ ሰው የተመሳሳይ ጾታ ኣፍቃሪ የማያውቅ ይመስለኛል፣ እኛ ግን ከጎናቸው ነን፣ ወንድም እህቶቻቸው፣ ወላጆቻቸው ነን፣ ሁሉም ቦታ ኣለን - ስም ያልተገለጸ





ኩዌር መሆን ምርጫ እንዳልሆነ ብዙ ሰዎች እንዲረዱ እመኛለሁ፤ ማንነታችን ነው። የእነሱን ግንዛቤ እና ተቀባይነት እንጂ ድጋፋቸውን ኣንፈልግም። - በጸሎት

## የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነትዎን ያከበሩት ወይም ኩራትዎን በአደባባይ የገለጹበት በጣም ያልተጠበቀ መንገድ ምንድነው?



ባለፈው አመት በኢትዮጵያ አዲስ አመት ዋዜማ ነበር ለታላቅ ወንድሜ የነገርኩት፣ በወቅቱ ትክክለኛ መስሎ የተሰማኝ ድንገተኛ ውሳኔ ነበር፣ እና ለአዲሱ ዓመት የነጻነት ጅምር ሆነ። - በጸሎት





የቀድሞ ፍቅረኛዬን በአደባባይ ሳምኩ፣ በእርግጥ ማንም አላየኝም፣ ግን ሰው መሀል ነበርን - ዮሃን

😂 የኮቪድ ጊዜ የባይ ባንዲራ ቀለማት ያሉበት ማስክ አርጌ ነበር። ሰዎች ግን የሚያምር የሮዝ እና ሰማያዊ ቀለማት መገጣጠም ብቻ ነው ብለው አስበው ነበር - ኬስ


ተስፋ የሚሰጥዎ ጥቅስ ምንድነው?
ምንም ያህል ጨለማ ቢሆን፤ ሁሉም ምሽት ቀን ይሆናል፤ ግፍ ሁሉ ወደ ሙዳቀት ይመራል ። - ግሎሪያ
ስለተረፍን ሀይል አለን፡፡ - ኬስ
የኦድሬ ሎርድ አባባል "ኃያል ለመሆን ስደፍር - ጥንካሬዬን ራእዬን እሙን ለማድረግ ስወስን - ፍርሃቴ ትርጉም እያጣ ይመጣል፡፡" - ሐበን